# ያሜሪካ ነፍሶች



(በቤይሩት፣ በጦርነት እሣት ውስጥ በስጋትና
በጭንቀት ላይ ላሉ ወገኖቼ ማስታወሻ)

በ «ኤፍ አስራስድስት»* ምድር ስትናወጥ፣
በቦምብ ውርጂብኝ አህዛብ ሲቀጠቀጥ
ያሜሪካ ነፍሶች በምድር የፀደቁ
ሣንድዊች እየበሉ እየተሳሳቁ ...
ከኖህ መርከብ ወጡ
ከእሣተ-ነበልባል ብቻቸውን ሊያመልጡ።

ምድር ስትታረስ
ሕንፃ ሲደረመስ፣
ህፃናት ሲቆሉ
በቦምብ ሲቃጠሉ፣
ንፁሃን ሲጋዩ
አይተው እንዳላዩ ...
በፍጥነት ተለዩ።

ነገውን እማያውቅ አሳቢ የሌለው፧
«የተኮነነች» ነፍስ ይዞ እሚዞረው፧

ምስኪኑም አበሻ
መጠለያ ሲሻ ...
ትንሽ ቁራጭ ዳቦ
ረሃብ ማስታገሻ ...

ያሜሪካ ነፍሶች በምድር የታደሉ
ከነጭ መርከብ ገብተው በደስታ ፏለሉ ...
ምስኪኑን አበሻም ጥለው ኮበለሉ።

ጌታቸው አበራ
(ሐምሌ 1998 ዓ.ም)

---

*F-16 ቦምብ-ጣይ ጄት